# ጾምና አምደ ሃይማኖት የሚለው መጽሐፍ ትምህርት

**የእድሉ ዮሐንስ ጋምሳ**

ማስታወሻ

**ጾም** ማለት መከልከል ማለት ሲሆን ራሳችንን ምንከለከለው ከምን እ ንደሆነ የጾሙትን አባቶቻችንን ከመጽሐፍ ቅዱስ እያነሳን እንናያለን ደግ ሞም ለምን እንደምጾሙ ጭምር እናያለን

....

“ሄደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ፥ ለእኔም ጹሙ ሦስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትብሉም፥ አትጠጡም እኔና ደንገጥሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን፤ ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ፤ ብጠፋ ም እጠፋለሁ።” — አስቴር 4፥16

፨ አስቴር እና ሌሎቹ የጾሙት (የተከለከሉት ) በስምምነት 3 ቀን ሙሉ ነ ው። ምንም ሳይቀምሱ ሳይጠጡ ወደ እግዚአብሔር ልመናቸውን አሰሙ ።

፨ አስቴር እና ሌሎቹ የጾሙት (የተከለከሉት )ለምንድነው ? ስንል እረፍ ትና መዳን ለአይሁድ ህዝብ እንድሆን ነው ።ለጾሙም መልስም አዳኙ አስቴር 6 ፣ 7 ይነበብ ።

*** ትኩረት * ነገር ግን የአስቴር ጾም ነው ብለው በመታሰብያነት የጾመ እስራኤላውያን የሉም ።**

የድንጋዩን ጽላቶች፥ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የተማማለባቸውን የቃል ኪዳን ጽላቶች፥ እቀበል ዘንድ ወደ ተራራ በወጣሁ ጊዜ፥ በተራራው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተቀምጬ ነበር፤ እንጀራ አልበላሁም፥ ውኃም አልጠጣሁም።” — ዘዳግም 9፥9

፨ ሙሴ ራሱን ለ40 ቀን ጾመ (ተከለከለ ) ምንም ሳይቀምስ ሳይጠጣ ፥ ወደ እግዚአብሔር ልመና አ ቀረበ ።

፨ ሙሴ ለምን ጾመ? ስንል ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ፥ ልመናውም ተሰማ ከእግዚአብሔርም ሁለት የድንጋይ ጽላት ተቀበለ ።

**"ትኩረት " ሙሴ ለ40 ቀን ጾመ በማለት በመታሰቢያነት የጾመ አንድም እስራኤላው የለም።**

15 ናታንም ወደ ቤቱ ተመለሰ። እግዚአብሔርም የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችውን ሕፃን ቀሠፈ፥ እጅ ግም ታምሞ ነበር።

16 ዳዊትም ስለ ሕፃኑ እግዚአብሔርን ለመነ፤ ዳዊትም ጾመ፥ ገብቶም በመሬት ላይ ተኛ።

...

23 አሁን ግን ሞቶአል፤ የምጾመው ስለ ምንድር ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እ ኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም አለ።2ኛ ሳሙኤል 12

፨እግዚአብሔር ሕፃኑን ቀሰፈው ፥ ዳዊትም ስለህፃኑ ወደ እግዚአብሔር ልመና አቀረበ። ምግብም፥ ም ጠጣም እምብ አለ (ጾመ) ፣

፨ ዳዊት የጾመው በግሉ ስለህፃኑ ነው እግዚአብሔር ግን አልሰማሁም ። ዳዊት ህፃኑ ከመሞቱ በፊት ጾ መ።

፨ዳዊት ህፃኑ ከሞተ በኃላ ጾሙን አቋረጠ ። ምክንያቱም ከሞተ በኃላ ምህረት የለምና ።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።” — ማቴዎስ 4፥2

፨ ኢየሱስ ምንም ሳይቀምስ ጾም 40ቀን ሙሉ ።

፨ ኢየሱስ ለምን ጾመ? ስንል ከፊት  የምጠብቀው ትልቅ አገልግሎት ስላለ በእግዚአብ ሔር ፍቃድ በብርታት ለመወጣት ጾመ። እንደ ጾመውም  የመጣበትን በድል ተወጣ በ ክብርም አረገ ።

**"ትኩረት " የትኛውም ሐዋሪያ ኢየሱስ እንደ ጾመ ብለው በመታሰቢያነት የጾመ የለም።**

“ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፥” — ነህምያ 1፥4

፨ነህምያ ጾም (ተከለከለ) ጀመረ ምን እንደ ጾመ የምግብ ዓይነት ይሁን ፥ ጭራሽ ምን ም ሳይቀምስ ይሁን መጽሐፍ ቅዱስ  አይነግረንም ።የምናውቀው ግን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ወደቀ ነው።

፨ነህምያ ለምን ጾመ ስንል የተፈራረሰውን እስራኤልን እንደገና ለማቋቋም በእግዚአብ ሔር ፊት ልመና አቀረበ። ልመናውም ተሰማለት ሰለሞን ከገነባውም በላይ ያማረ ሆነ።

**"ትኩረት " ነህምያ እንደ ጾመ ብለው የጾመ እስራኤላዊ የለም።**

“በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ፥ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው።”— ሐዋርያት 14፥23

፨ሐዋሪያት ለቤተክርስቲያን ሽማግሌ ለመሾም ይጾሙ እና ይጸልዩ ነበር

**"ትኩረት "ሐዋሪያት  ጾመው እንደሾሙ ፤ በመታሰብያነት እንጾማለን የምል ክርስቲያን አልተነሳም ነበር።**

“ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ።”  — መዝሙር 109፥24

፨ዳዊት ስጾም የምግብ ዓይነት እንደጾመ እናያለን ።

፨ ለሎች ደግሞ ምንም ሳይቀምሱ እንደጾሙ እናያለን ።

**<u>ጾም  ከዓላማ ጋር እንጂ ከምግብ ጋር አይደለም ማለት ነው።</u>**

፨  ስለጾም ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተማማርን ስለ  ''አምዴ ተዋሕዶ መጽሐፍ ''አጾዋማት እንያ .....

# ከሰባት ዓይነት አጽዋማት" አንዱ አብይ ጾም "ይባላል

"ይህ ጾም ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀን እንደ ጾመ ፥ ድያብሎስን ድል እዳደረገው በእር ሱ አርአያነት እንጾማለን የምል አጽዋም ነው "

ከሆነ የምከተሉትን መልሱ !?

፨ ኢየሱስ ድያብሎስን ድል ለመንሳት ጾመ ፤ ድልም ነሳ ሞትን በሞት ሻሬ። ታድ ያ እኛ ምንጾመው መዳናችንን ለመጠበቅ ወይስ ሞትን በሞት ልንሽር ?

፨ ኢየሱስ ስጾም ተፈተነ ፈተናውም በድል አለፈ ! በድል ስላለፈ ቀጣዩን አገልግሎት ጀመረ እንጂ የጾሙ ማብቂያ የአገልግሎቱ መጨረሻ ሳይሆን መጀመሪያ ነው። እኛስ ምን ለመጀመር ነው የምንጾመው ?

፨ደግሞ እኛ የአሁኖቹ ከቀደሙት ከሐዋርያት አንበልጥም ፤ የኢየሱስ ጾም ብለው ለምን አልጾሙም ?

፨ ኢየሱስ የጾመበት ዓላማና የእኛ የእርሱ አርአያ ነው ከምንለው ጋር ምን ግንኙነት አለው ?

፨ የእርሱ አርአያ ከሆነ ኢየሱስ ስጋ ፣ ቅቤ ነው የጾመው ....?

፨የእርሱ ከሆነ ጾሙን ፈታን ስንል በጠጅና በሀረቀ ነው ጾሙን የጨረሰው ኢየሱስ ?

፨ የጾሙ መጨረሻ ፦ '' ይህን ለምን አልችሁ?'' ብላችሁ ፈታችሁን ለማቅላት ነ ው ጥርሳችሁን ለማቀጨጭ ነውን ?

## በሁለተኛነት የምጠቅሰው ጾም የሐዋርያት ጾም የምባለው ነው

" ይህ ጾም ሐዋሪያት መንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኃላ ለወንጌል ስራ እንድሰምርላቸው የጾሙት ጾም ነው።እኛም ይህንን ለማሰብ እንጾማለን የምል ነው"

ከሆነ የምከተሉትን መልሱ !?

፨ ሐዋሪያት ለተለያየ ዓላማ እንደምጾሙ ምንም ክርክር የለም። ይህ ሀሳብ ግን መ ንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኃላ ስብከተ ወንጌል ከመጀመራቸው በፊት የጾሙት ጾም ነ ው የምል በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽር ስታይ ውድቅ ይሆናል ምክንያቱም ሐ ዋሪያት መንፈስ ቅዱስ ከመቀበላቸው በፊት በፀሎት ይተጉ እንደነበሩ ሐዋ 1 ፥ 13-1 4 ማየት ይቻላል ።ሐዋሪያት መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደ ለስብከት ወጡ እንጂ ሌላ ሀ ይል ስጠብቁ አናይም ሐዋ 2። ስለዚህም ማስረጃ አልባ ፈጠራ ነው።

፨ ደግሞም አዎ ጾመው ነበር ብባል እንኳን መጾም ያለብን ለማሰብ ሳይሆን ኃይልን ለመታጠቅ መሆን አለበት።

፨ለማሰብ እስከ ጾምን ድረስ ከመገረም ውጭ እነሱ በሄዱበት መንፈስ እንድንሄድ አያደርገንም ።

**፨ለክርስቲያን መውጣትና መስበክ እንጂ መታሰቢያ ኃይል አይሆንም ።**

## በ3 ኛ የምጾው "ጾመ ፍልሰታ" የምል ነው

"ይህ ጾም የኢየሱስ እናት ከሞተችበት ተነስታ ስታርግ ቶማስ በማየቱ ለሎች ሐዋሪያት ባለማየታቸው ማየት አለብን ብለው ከነሐሴ 1-15 የጾሙት ጾም ነው።እኛም የተሰወረው መንፈሳዊ ምስጢር ለቤተክርስቲያን እን ድገለጽ እያለን እመቤታችንን እናስባለን ።" የምል ነው

ከሆነ !?

፨ይህ ሁሉ ተረት ግን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የለውም !

፨ ከእምነት አባት ከአብርሃም እግዚአብሔር እንደ ልቤ ያለው ዳዊት ... እነሱ በመቃብር እያሉ የኢየሱስ እናት ብቻዋ እንዴት አረገች?

፨ አይሁድ 'ይቺ' በማለት የኢየሱስን እናት ይንቃሉ እንጂ ለነሱ ማርያም ፍርሀት ሆና አታቅም። ፍርሀት ልት ሆን ብትችል ወደ መስቀሉ አጠገብ አያደርሱም ነበር። በህይወት ስጋ እያለች ሳይፈሩ እንዴት ስትሞት ፈሩ?

፨ ኢየሱስ እኮ የመጨረሻው መገለጥ ነው በቃ ። የምን መገለጥ ፈለጋችሁ ሌላ?“ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግ ሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤”— ዕብራውያን 1፥2

፨ ዓለም የናቀችሁ ምስጥር ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደሆነ አታቁውምን ? 1ቆሮ “ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።” — 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥24

፨ ማነው እሷን በማሰብ መንፈሳዊ ምስጢር ይገለጻል ያለው ?

፨ ሁሉም ነብያትም የአድስ ክዳን ሐዋሪያትም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በእግዚአብሔር ፊት በመውደቃቸ ው ጸሎታቸው ተሰማላቸው። ግን ምንም ማስረጃ የለም በሞተ ሰው ፊት ስለወደቀም፤ ወድቆም ስላገኘው ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ?

፨ በእግዚአብሔር ፊት ብትደፉ የት በደረሳችሁ ግን ፉጡር ስሪ መውደቃችሁ እግዚአብሔር ለማይረባ ዐይዕ ምሮ አሳልፎ እንደሰጠ እንረዳለን ሮሜ *2*

# 4 ኛው የነብያት ጾም ይባላል

"ይህ ጾም ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ይመጣል እያሉ በናፍቆት ስ ጠባበቁ የጾሙት ጾሙ ነው ።እኛ የነብያትን የጾም ድካም ለማሰ ብ  እና እንደ ነብያት ሀይልን ለመቀበል እንጾማለን " የምል ነው

ከሆነ የምከተሉትን መልሱ !?

፨ ከነብያቱ የተኛው ጾመ ብንል  ብያንስ አንድ ነብይ እንደ ማስረ ጃነት ብኖር  መልካም ነበር !? ግን የለም

፨ ስቀጥል ለማሰብ ተብሎ መጾም ..እንዴት እንደምከብድ በማ ለት እንደት ቻሉት ብለን በመገረም በእነሱ እግርህ ስሪ ለመጣል ብቻ ነው።

፨ የሌለ ነገር አትፈልጉ ከመጽሐፍ ቅዱስ !?

# 5 ኛው ገሀድ ይባላል

ገሃድ ማለት ግልጽ ማለት ስሆን የምጾመው ከጥምቀት በፊት ባ
ሉ ቀኖች ነው።

፨ ደግሞ ማስረጃ አላችሁ ? ምንም የለም !

፨ ይህ ጥምቀት የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የምትጠ
መቀው ሳይሆን ዮሐንስ ጥምቀት በመባል ሎሚ   የምወረወር
ብት በዓል ቀን በፊት የምጾም ለማለት ነው።

፨ አምነን ከመጠመቃችን በፊት የሚጾም ብሆን እሰይዮ ግን ጥ
ምቀት አንድት  ናት እየተባለ ከመዝለል ባላለፈ ነገር ላይ ለምን
አስፈለገ ?

አዎ ታጥበ ለመቆሸሽ ለምን አስፈለገ  መጾም ? ማታ ውሎአቸ
ው  ይመሰክርልናል ።

# 6 ኛው የነነዌ ጾም ይባላል

" በዮናስ መጽሐፍ ታርኩን እናገኛለን  ወደ  እግዚአብሔር  በጮ
ኹ ግዜ እግዚአብሔር እንደ ሰማቸው እና እኛንም ይሰማናል በ
ማለት አንድ ግዜ ጥር ወይም የካቲት ይጾማል ።

፨ ጾሙ መልካም ነው።የነነዌ ሕዝብ  ግን በግዜው ለተፈጠረው
ችግር ወዲያው በእግዚአብሔር ፊት ወደቁ ።ታድያ እኛ ጥርና የ
ካትት እየጠበቅን መውደቅ አለብን ?

፨ እግዚአብሔር ይሰማል ይመልሳል ጥርም የካትትም አያስፈል
ግም?

፨ ምክንያቱም ጾሙ በእግዚአብሔር ፊት  መውደቅ እንጂ መታ
ሰቢያ አይደለም ።

# 7 ኛው ራብዕ እና አርብ ይባላል

ዕለት "ራብዕ ኢየሱስ የተሸጠበት ቀን ስለሆነ ለማሰብ ነው ።ዕለት አርብ ደግሞ ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀን ሲለሆነ ለማሰብ ይጾማል ።"

....

፨ታድያ እነዛን ቀናት ቅቤ ነክ የምያወፍሩ ምግቦችን በመከልከል ይጾማል ፣ በተቃራኒው ደግሞ ጫት ስጋራ መጠጥ እንደ ጾም አይታሰብም ለመጾምም የምያስብ ህዘብም የለም። ቅበ ነክ ነገር መተው ከስጋ ሀሳብ ነፃ አላረጋቸውም ።ጥቅሙ ምንድነው ?

ስጠቃለል

የተዋሕዶ ጾም ከመታሰብያነት በዘለለ ከሀጢአት ለመንጻት የምደረግ ወይም ለመመለስ የምደረግ መከልከል አይደለም ።በመታሰብያነት እገሌ እንደ ጾመ እጾማለሁ ከማለት ውጭ ምንም ዛሬ ላይ ጌታ ምን ይለኛል የምል ጥያቄ ፈቃዱን የ ማወቅ ጥያቄ አይታይም ። የመጽሐፍ ቅዱሱ አጾዋማት እና የተዋሕዶ አጾዋማት ተመሳሳይነታቸው "ጾም" የምለው ፍደ ል ብቻ ነው። ስጾም ለምን እንደምጾም ከጾሙ በኃላ በማግስቱ የተለወጠ ማንነት ሳይሆን ጭፈራ ቤቶች ስጨናነቁ ነው የምናየው ምክንያቱም ጾም ለነሱ መታሰር ስለሆነ ። ዓላማው "መታሰቢያነት " ብቻ መሆኑ ሰውን ልቀይር አይችልም አ ይቀይሩም።

ጾሙ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፀጋ ሳይደገፉ 50% እኔ 50% ፀጋ ማለታቸው ከኃጢአት ነፃ ማውጣት አልቻለም ። ም ክንያቱም ፀጋ ጥንቁልናን ድግምትን ይቃወማል ለተዋህዶ ተከታይ ይህን ብትነግረው ፊቱን ያጨልምብሃል። ራሳቸውን በማኮላሸት ብሞኖክሱም ግን ከኃጢአት ነፃ መሆን አልተቻለም ።

ፀጋ ስራው ይህ ነው

11 ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤

12-13 ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የ መድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመ ምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ ቲቶ 2

እንዴት እንጾም ?

ኢሳይያስ 58

3 ስለ ምን ጾምን፥ አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለ ምን አዋረድን፥ አንተም አላወቅህም? ይላሉ። እነሆ፥ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፥ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ።

4 እነሆ፥ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ፤ ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደም ትጾሙት አትጾሙም።

**፨ ነብያት ሐዋሪያት ስጾሙ በእግዚአብሔር ፊት ወደቁ ;እንጂ ፍጡር ጋ የወደቀ የለም ;ለዚያውም በስጋ ወደ ሞተው ።**

" ተባረኩ ለቃሉ ብቻ እንወግናለን "